# አንድ ህዝብ ማግኘት የሚገባውን መሪ ያገኛል?

ከገታቸው ኃረደው

ከላይ የተጠቀሰውን አርእስት ደጋግመን ብናነበው አባባሉ ትክክል ይመስላል፣ አንድ መሪ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ወደ ህዝቡ ቀርቦ ከተዋወቀ በኋላ የሱን ፍላጎት የሚፈልጉትን መርጠ ስለ አገር ጉዳይ በጥቂቱ ነግሮ ስሜታቸውን በመረዳት የሚጠቅሙትን አቅርቦ የማይፈልጋቸውን ካገለለ በኋላ ያቀረባ ቸውን ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በመመርመር የሚፈልጉትን ሲሰጣቸው ጥቅም ገንዘብና ሹመት ፈላጊዎቸን በጣም ሲያስደስታቸው ከሱ ጀርባ ዶልተው ሴራ እንዳያደርጉበት እርስ በእርሳቸው እንዲ ሳለሉ ሲያደርግ በመካከላቸው አለመግባባት እንዲፈጠር ሲያነካክሳቸው አንዱ ከሌላው የበለጠ ታማኝ ለመሆን የሌላውን ምስጢር ለገታው በመንገር ጥርስ እንዲነከስበት የድርጋል፣ አዲሱ ጌታ በነጋደውም በሰራተኛውም ተወዳጅ እንዲሆን የሚችለውን ጥረት ይደርጋል፣ ስራው ሁሉ የተንኮል ስለሆነ ሹማምንቱን በየጊዜው በመለዋወጥ ሲበውዛቸው ይህ ችግር እንዳይደርስባቸው ፈሪዎችና ታዛዦች ስለ ሚሆኑ አዲሱ ጌታ ቀስ በቀስ እምባ ገነን ይሆናል፣ እነዚህ ቅጥረኞች አዲሱን አለቃቸውን በየስፍራው እየሄዱ ያሞግሱታል ያወድሱታል፣ አፈ ታሪክ ፈጥረው ያወሩልታል፣ ትናንትና ማን መሆኑ ያልታ ወቀው በጥቂት ጊዜ ውስጥ የልብ ልብ ስለሚሰማው፣ ትእቢትና ንቀት ይከተሉና የቀድሞ አገልጋዮቹን በጣም ሲያርቃቸው በተለይ ተራ ሰው በነበረበት ጊዜ የሚያውቁትን አንድ ዘዴ ፈጥሮ ከህዝብ ጋር እንዳይገናኙ ያደርጋቸዋል፣ አምባ ገነንን መሪን ያሚፈፈጥረው ራሱ ህዝቡ እንጂ መሪው ብቻውን አይደለም፣ የንጉስ ሀያለ ስላሴን የስልጣን አመጣጥ መለስ ብለን ብናነብ የተጠቀሙት በዚህ ዘዴና ምህረተ ቢስና ጨካኝ በመሆሁናቸው ነብር፣

ንጉሱ የማይገባቸውን ዙፋን ለመውረስ ብዙ ባላንጥዎችን አጥፍተዋል፣ በተለይ ደጃዝማች ተበለው ካተሸሙ በኋል ብዙ ህዝብ አስገድለዋል፣ ከዙፋን ተቀናቃኝ ከንጉስ ሚካኣል ጋር ባደረጉት ጠርነት በራሳቸው ዝማቾች ካስፈጁት ህዝብ የበለጠ የንጉስ ሚካኤል ዘማቾች በራያና በአዘቦ ተዋጊዎች ብዙ ህዝብ አልቋል፣ ንጉስ ህይለ ስላሴ አንድ ጠባይ ነበራችው፣ አንድ የመንግስት ሰራተኛ የመንግስት ገንዘብ ቢያጠፋ ወንጀል ቢሰራ፣ ያጠፋውን ገንዝብ እኛ እንከፍልለታለን ላጠፋው ጥፋት ምረነዋል በለው ሲለቁት ገን በሳቸው ሰልጣን ላይ ከመጣ በለው ግረፈው ብለው አርባ ጅራፍ ያስገርፉታል፣ አንድ ሰው ንጉሱን ካማ የሳቸውን እምባ ገንነት ከተናገረ፣ ክብር ነካ ዘለፋ ተናገረ ተብሎ ሲከሰስ አንድ ባልስልጣን ጉዳዩን እንዲከታትል ሲያዙ፣ የታዘዘው ሰው ተከሳሹን አስር ቤት እስኪከተው ውይም እስኪጠፋ ድረስ አረፍት አያገኝም፣. ስልጣናቸውን የተቀናቀነ ሰው የሞት ፍርድ ፈርደውበት መሞቱን ለማረጋገጥ በልዩ መኪና ወደ መስቀያው ስፍራ ሄደው ይመለከታሉ ፣ ይህንን በበላይ ዘለቀና በመንግስቱ ንዋይ ስቅላት ተመልክተናል፣ የታህሳስ 5 ቀን 1953 ንቅናቄን መርተው ክጦር ስራዊቱ ጋር ተዋግተው ጥይት ስለአለቀባቸው፣ መንግስቱ ቀስሎ ሲያዝ፣ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ሻምበል ባዬ ጥላሁን እቶ ገርማሜ ንዋይ ራሳቸውን ሲገሉ አስከሬናቸው ቤተ መንግስት ተወስደ ንጉሱ ከተመለከቱ በኋላ አስከሬናቸው በአደባባ እንዲሰቀል አዘዙ፣ አንድ ሰው ክሞተ በኋላ ክብር ስላለው በሰነ ስራአት መቀበር ሲገባው ክርስቲያን ነኝ የሚሉ ንጉስ እንዲህ ያለ አረመኔ ስራ ሲሰሩ አቡነ ባስልዮስ ንጉሱን አልገዘቱም፣ ያምንወደውና የሚወደን ህዝባችን እያሉ የኢትዮጵያን ህዝብ መሬት እያሳሙ ስለገዙት ህዝቡ ባለወለታቸው እንዲሆን ይፈልጋሉ፣ ስለንጉሱ ጨካኝነት አሪአና ፋላቺ ያተባለች የጣሊያን ጋዜጠኛ በ 1966 በደረገቸው ቃለ መጠይቅ ንጉስ ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል፣የነጋሲ ዘር እንደመሆናችን መጠን ስልጣን የባህርይ ገንዘባችን ነው፣ . አንድ ንጉስ በሀይል በመጠቀሙ ሊጸጸት አይገባውም፣ ቆራጥ እርምጃ ለመውሰድ ወደ ኋላ ብለን አናውቅም፣ ለህዝቡ የሚበጀውን የሚያውቅ ንጉሱ ነው፣ ህዝቡ ራሱ አያውቀውም፥ አጼ ሀይለ ስላሴን ከራሳቸው የበለጠ የሚያውቃቸው ስለ ሌለ ምን ያህል ጨካኝ መሆናቸውን ራሳቸው መስክረዋል፣

ጃንሆይ እርጅናን ሲሸሹ ሞት ባልጠበቁት መንገድ ስለመጣባቸው ስጋቸውንና ታሪካቸውን ገለው የእጃቸውን ዋጋ ከፈሉ፣ ከዚህ ሌላ ንጉሱ በኢትዮጵያ ህዝብ የፈጸሙት ይቅርታ የማይገባው በደል አለ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት እቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ኤሬትሪያን ከኢትዮጵያ ጋር በፌደራል አመራር ለመቀላቀል በከፍተኛ ጥረት ተስክቶላቸው ጥቂት አመታት ክቆዩ በኋላ

የፌደራሉ አመራር ተሰርዞ ሙሉ ውህደት እንዲደረግ ንጉሱ አዘዙ፣ ንጉሱ የህንን ለውጥ ለማድረግ ያተገደዱት በኢትዮጵያ ያሉ ግዝቶች ሁሉ ለኤሬትሪያ የተሰጠው የውስጥ አስተዳደር መብት ለእኛም ይሰጠን ስለሚል ፌደራል የሚለው ቃል መሰረዝ አለባት ያሉት ከፍራቻ የመጣ አስተሳሰብ ነበር አቶ አእክሊሉ ይህንን እንድሰሙ ይህ መሆን አይገባውም ስለ ፌደራሉ ስምምነት መፍረስ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በቅድሚያ ሳያውቀው በተግባር እንዳይውል በአንቀጽ 91 ስለተከለከለ ፌደራሉን በሙል ውህደት ለመወጥ ማሰባችንን ለድረጅቱ ብቅድሚያ መንገር ይገባናል፣ ይህንን ሳናደርግ የድርጅቱን ውሳኔ ከተውነው ለመወጣት የማንችለው ችግር ውስጥ ከመግባታችን ሌላ የአለም ህዝብ ይፈርድብናል በማለት አቶ አክሊሉ ለስብሰባው ሲገልጹ. ንጉሱ በቁጣ አነጋገር አንተ የታዘዝከውን ፈጽመህል የቀረውን ለእኛ ተወው ሲሉ፣ በስብሰባው የነበረው የአሜሪካ አምባሳደር የህ ችግር አያመጣም ጉዳዩን ስለምከታተል ለእኔ ተዉት በማለት ስብሰባውተፈጽመ፥

ንጉሱ እንድፈለጉት ፈደራል ተሰርዞ ውህደት በታወጀ ማግስት አሬትራውያን በመላ አረብ አገሮች መጬህ ጀመሩ፣ የነሱ ጭኸት፣ሰሚ ስለአላገኘ ትግል ቀጥለው በከሃዲው በመለስ ዜናዊ ፍቃድና ትብብር አሬትራውያን ነጻነታቸውን አወጁ፣ አቶ አክሊሉ እንዳስጠነቀቁን የማንወጣው ችግር መጣብን ፣ የኢትዮጵያ ግዛቶች እንደ ኤሬትራውያን መብት እንዳያገኙ ንጉሱ ኤረትሪያን ከኢትዮጵያ ጋር በሙሉ ውህደት ስለቀላቀሉ በታሪክ ለመመስገን ላደረጉት ስህተት ዛሬ እኛ ዋጋውን በህይወታችን እየከፈልን ነው፣ ችግሩ የምንወጣው ስለአልሆነ የልጅ ልጆቻችን ለረጅም ዘመን ደማቸውን ማፍሰስ ይገደዱ ይሆናል፣ ኢሳይያስ አፈወርቂ ለኢትዮጵያውያን ለመቶ አመት የሚሰሩት ስራ እሰጣቸዋለሁ ብሎ አሹፎብን ነብር፣ ንጉስ ሀይለ ስላሴ በሺህ አመታት ሰርተን ማንጨርሰው ስራ ሰጥተውን አለፉ፣ የፈደራሉ ስምምነት ፈርሶ ውህደት እንዲመሰረት በተደረገው ስብሰባ የአሜሪካ መንግስት አምባሳደር ንጉሱ በዚህ አቅድ እንዲገፉበት እንዳልገፋፋ ሁሉ ብ1981 ኤሬትሪያ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል የረዳው ከዚህ አመተ ምህረት ጀምሮ እስከ ዝሬ ድረስ ቅጥረኛውን መለስ ዜናዊን መሳሪያና ገንዘብ እየሰጠ የሚያስጨርሰን የአሜሪካ መንግስት ነው፣ንጉሱ ፈደራልሉን ትተው ሙሉ ውህደት እንዲያደርጉ የአሜሪካ አምባሳድር ከገፋፋቸው በኋላ በለውጡ የአሜሪካ መንግስት ኤሬትሪያ ውስጥ ቃኘው ሻለቃ የሚባለውን የጦር ሰፈር እንዲከፍት ንጉሱ ፈቀዱለት.፣ በአገሪቱ ውስጥ ለሚንቀሳቀሰው ማናቸውም ነገር ተጠሪው ተመስጋኙ አሳቸው ነበሩ እኛ ምንም አልሰሩም አንልም ግን በአርባ ሶስት አመታት ዘመነ መንግስታቸው ሌላውን ትተን ከፋሽሽተ መንግስት ጋር ብናውዳድረው ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር እያተዋጉ ከሰቸው የአርባ ሶስት አመት ስራ በጣም የበለጠ ሰርተዋል ጣሊያኖች በአምስት አመት ቀይታቸው መንገድና ህንጽዎች ሲሰሩ ጃንሆይ መንገዱ እንዲሰፋፋ እንዲታደስ ምንም ያደረጉት ነገር የለም.እሳቸው ያተኮሩት ህንጻው ቤቶች ላይ ብቻ ነው፣ድል አድራጊ ተብለው ከተመለሱ በኋላ የመንግስት ንብረት የጠላት ንብረት በማለት ለሁለት ከከፈሉት በኋላ የጠላት ንብረት የሚባለውን ጣሊያኖች የገነቡትን ህንጻ በራሳቸውና በቤተ ሰቦቻቸው ስም በርስተ ጉልትነት በግል ይዘው እስከ እለተ ሞታቸው በየወሩ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ይካብቱ ነበር. የመንግስት ንብረት የሚባለው ከጦርነቱ የተረፍ ደሳሳ ጎጆዎች ናቸው፣ ከጠርነቱ በኋላ በብዙ ሽህ የሚቆጠር አርበኞች መጠለያ መቋቋሚያ አጥተው በረሃብ ይሰቃዩ ነበር፣ ንጉሱ ሸሽተው ሲሄዱ የተዋጋውአርበኛው ነበር ጠላትን በአይናቸው ሳያዩት የጠላትን ንብረት ወርሶ አርበኛን ማስራብ እጅግ አሳፋሪና ውለታ ቢስነት ነው፣ በጠላት ዘመን ሰላይና ባንዳ የነበረው ሀሉ ሹመትና የአርሻ መሬት ከንጉሱ ሲሸለም እውነተኛው አርበኛ እስታዋሽ ስላእጣ ባዶ እጁን ቀረ. ኢትዮጵያ.አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ቅርቶ የገደለሽ በላ የተባለው በዚያን ዘመን ነው፣

ንጉሱ ገንዘብ በጣም ይወዳሉ በቃኝን አያውቁም ከህዝብ እያዘረፉ ስዊዘርላንድ ባንክ ያከማቹትን ባንኮች እንደልማዳቸው ንጉሱ አላስቀመጡም ብለው ሲክዱ ከሳቸው እረፍት ብኋላ ተመርመሮ ተገኘ የተባልውን ገንዘብ ልጃቸው አእልጋ ወራሽ አሰፋ ወሰንና መንግስቱ ሀይለ ማርያም ሲከፋፈሉት አልጋ ወራሹ ያለ ህዝብ ያለ አገር ያለ ጳጳስ ዘውድ ደፍተው አጼ ተብለው ሲነግሱ የእንግሊዝን ንጉሳዊ ቤተ ሰቦች ጋበዙበት፣ መንግስቱ ሀይለ ማርያም ዝምባዌ ውስጥ ያርሻ መሬት ገዛበት ይባላል ንጉሱ ከህዝብ የዝዘረፉትን ገንዘብ በአገር ቤት ቢያስቀምጠት አንድ ቀን ህዝብ ስለሚሰማ.፥ ገንዝቡን በጣም ራቅ የለ ስፍራ ላኩት.፣ ገንዘቡን የላኩት በዚያን ዘመን ያአሜሪክ ፐረዝዳንት ለነበሩት ሙሴ ዎርዲንግ

ሲሆን በደብዳቢያቸው ፕሬዘዳንቱን የለመኑት ከአባቴ ጀምሮ በአእሮፓ የተቀመጠውን ገንዘቤን በአሜሪካ ባንክ ውይም በትልልቅ ኩባንያዎች እንዲያስቀምጡልኝ እርዳታዎን እንዲያደርጉልኝ የሚል ነው፣ ንጉሱ ይህንን ደዳቤ የጻፉት እልጋ ወራሽ በነበሩበት ጊዜ በ 1916 ነው፣ ንጉሱ ከህዝብ እየዘረፉ ያጠራቀሙት ሀብት ከቤት እልፎ ባአድ አገር ተላክ፣ ይህ የጠላት ንብረት የሚባለው ሀብት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ህንጻዎች ሲሆኑ ይህንን ያስተዳድሩ የነበሩት የንጉሱ ሴት ልጅ ልእልት ተናኘ ወርቅ ነበሩ፣ ልእልቲቱ በጣም ቀጣቢ ነበሩ ይባላል፣ በንጉስ ሀይለ ስላሴ ዘመን ኢትዮጵያ የአንድ ቤተሰብ ንብረት ነበረች፣ ይህ ሁሉ ሃብት እያለ በሺህ የሚቆጠረው የወሎ ህዝብ ሲያልቅ ህጻናት የሞቱትን እናቶች ጡት ሲጠቡ ማየቱ ልብን ይሰብራል፣ በመጨረሻ ደርግ መጣና ሁሉንም ሲውርስ ከዚያመለስ እጅ ስለገባ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብቱን ተነጥቆ የበላተኛ ተመልካች ሀኖ ይኖራል፣ ይህንን የአጼ ሀይለ ስላሴን ታሪክ ከሰማኒያ አምስት አመታት በኋላ ለህዝብ መገለጹ ብዙዎችን እያስደሰት የሆናል፣ይህንን ያደረግነው ሟችን ለመውቅስ ወይም መልካም ስራቸውን ለማጉደፍ ሳይሆን የምንወደውና የሚወደን ህዝባችን እያሉ በዚያን ዘመን የነበረውን ህዝብ እንደእንስሳ እየነዱ እንደገዙት የዛሬው ትውልድ እንዲያውቀው ከነማስረጃው ማስረከብ የታሪክ ግዴታች ስለሆነ ነው፣ ንጉሱ ለአሜሪካ ፕሬዜዳንት የላኩትን ደብዳቤ እንባቢ እንዲመለከተው ከዚህ ጽሁፍ ጋር በአባሪነት እያይዝነዋል ፥

መንግስቱ ሀይለ ማርያም ንጉሱን ክስልጣናቸው ካስወገደ ብኋላ አስታራቂ መስሎ የኢትዮጵያን ተማሪዎች በማታለል ስልጣኑን ነጥቆ ከወሰደ ብኋላ ደርግ የሚባሉ ነፍሰ ገዳዮች ሰብስቦ ወጣቲን ሆነ አዛውንቱን ሳይለይ የፍየል ወጠጤ እያዘፈነባቸው ከገደላቸው ብኋላ ወላጆች የልጆቻቸውን አስክሬን እንዲገዙ አስገደዳቸው፣ መንግስቱ የገደላቸው ሰዎች ምንም ጸጸት ወይምየሀሊና ወቀሳ ስለአልተሰማው እኔ እንኳንስ ሰው ትንኝም ገድዬ አላውቅም እያለ ሲያሾፍብን ከርሞ በመጨረሻ የህዝቡን ወኔ ሰልቦ ፈሪ አድርጎ ወደ ዝምባዌ ኮበለለ፣ የኢትዮጵያ መሪዎች ህዝቡ በጠላት ሲወረር ህዝቡን ለጠላት አስረክቦ መፈርጠጥ የተለመደ ስለሆነ የመለስን መፈርጠጥ በቅርቡ እንደምንሰማ ተስፋ አለን፣ የመንግስቱን ወንጀል በአንድና በሁለት ገጾች ለመግለጽ ስለማይቻል ለታሪክ ጸሀፊዎች ትተን ስለ መንግስቱ ደቀ መዝሙር ስለመለስ ዘናዊ እንነጋገር መለስ በአሜሪካ ፍቃድ በሻቢያ እርዳታ በኦኔግ አጃቢነት በ 1981 ጓዙን በአህያ ጭኖ ጀሌ ወታድሮቹን አስከትሎ ኢትዮጵያን ከወረረ በኋላ ሁሉም በጎሳ ይደራጅ፣ በአንደነት ለመኖር ያልፈለገ ተገንጥሎ ለመሄድ ይችላል ከማለቱ ሌላ መገንጠል መፈቀዱን በህገ መንግስቱ በአንቀጽ 39 አረጋግጧል፣ የአገሪቱ መንግስታዊ አእመራር በፈደራል ስለሆነ በጎሳ የተደራጁት ዜጎች የክልል አመራራችውን የፌደራሉን መንግስት በቅድሚያ ሳያስፈቅዱ ለማስተዳድር ሲችሉ በክልላቸው የሚሰበስቡትን ጊቢ ለክልሉ መተዳደሪያ ለማውጣት መብት አላቸው ግን ከገቢያቸው የተወሰና ገንዘብ ለፈደራል መንግስት መክፈል ይገደዳሉ፣ የፌደራሉ አመራር ይህ ሆኖ ሳለ መለስ የክልል መሪዎቸን በማታለል በክልላችሁ ተወስናችሁ መቀመጥ አያስፈልጋችሁም ሁላችንም በአንድነት ብንሰራ ፣ኤኮኖሚያችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ልናዳብር ስለምንችል እንቀራረብ በማለት እንደጥምር መንግስት በማስመስል ስሙን ኢህአዴግ ብሎ ሁሉም በተለጣፊነት እንዲመዘገቡ አስገድዶ ካስፈረማቸው በኋላ የክልል መሪዎች፣ አንደኛ የግል ጥቅማቸው እንዳይቀርባቸው፣ሁለተኛ ንብረታቸውን ወርሶ እንዳያስራቸው የመረጣችውን ህዝብ ክደው ከወያኔ ጋር አብረው ይሰራሉ፥

ሁለቱ ትልልቅ ድርጅቶች አማራና ኦሮሞዎች ሲሆኑ ሁለቱ በምክር ቤቱ ክሶስት መቶ ሃምሳ በላይ አባላት ሲኖራቸው መለስ በትግራይ ክልል ያስመረጠው ሰላሳ ዘጠኝ አባላት ብቻ ናቸው መለስ እነዚህን በጣት የሚቆጠሩ አባላት ይዞ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ህዝብ ያስተዳድራል፣ ይህ ትክክል አይደለም፣ ይህንን መቆጣጠር የሚገባው የምርጫ ቦርድ ነበር፣ አስከአሁን አላደረገም፣ መለስ የምርጫ ቦርዱን ሀላፊነት ነጥቆ ሁሉንም የሚቆጣጠረው እሱ ራሱ ስለሆነ ይህ እንዳይደገም የውጭ አገር ታዛቢዎች ከመራጩ ህዝብ ጋር በመተባበር ማስለውጥ ይችላሉ፣ በ 1997 ምርጫ ምክትል የምርጫ ቦርድ ሀላፊ የነበረው ተስፋዬ መንገሻ በሚያዚያ ወር ስለሚደረገው ምርጫ ሲናገር የ 1997 ምርጫ ፍጹም ትክክል ስለነበር የሚያዚያውም ትክክለኛ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ፣ በተለይም አሁን እኔ የምርጣው ቦርድ ሀላፊ ስለሆንኩ የምርጫው ውጤት ትክክል ስለሚሆን ደስ ይለኛል ይላል፣ የ 97 ምርጫ መለስ አጭበርብሮ አሸነፍኩ እንዳለው ሁሉ የሚያዝያ ምርጫ

መጭበርበሩ ስልማይቀር ይህ ሁሉ ችግር ለምን አስፈለገ? ምርጫው የሚደረገው መለስን ለማስደሰት ስለሆነ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር በከንቱ ከማውጣት ለኤድስ ብሽተኞች.በወባና በሳምባ ነቅርሳ ለሚሰቃዩ ወገኖቻችን መርጃ ቢሰጥ መለስም የመንፍስ ደስታ ይሰማው ነበር፣

መለስን በስልጣን ለማቆየት ዋናው መሳሪያ የምርጫ ቦርድ ሀላፊዎች ሲሆኑ፣ ሁለተኛው የመከላከያ ሰራዊታችን ነህ. አንተ ወታደሩ ክ1927 ጀምሮ የመሪዎች ታማኝ አገልጋይ በመሆንህ ህዝቡንና ራስህን እያስገደልክ፣ በማያገባህ ጦርነት ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ ሆነህ ተገለህ አስከሬንህ ሲጎተት ውሻ ሲጫወትበት ስላሳና አርባ የምትሆነው በአንድ ጉርጓድ ስትቀበር አንገትህ ላይ ያለው መታወቂያ ምልክትህ አብሮህ በመቀበሩ ሚስትህና ልጆችህ መኖርህና መሞትህን ስለማያውቁ አድሜ ልካቸውን እርማቸውን ሳያወጡ.ከዛሬ ነገ ትመጣለህ በማለት ቀንና ሌሊት እያለቀሱ ሲጠብቁህ፣ ጎረቤትህ የሱማሌ ህዝብ ሳይደርስብህ በጸብ ሳይፈልግህ ለመለስ ጥቅምና ስልጣን ሚስቱንና ልጆቹን እየገደልክ ስለምታ ሰቃያቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ የደም በቀል ጊዜ ጠብቆ ይሚፈነዳ ቦንብ አዘጋጅተህለታል..

ወንድም የኢትዮጵያ ወታደር.......ይህን ያህል የምትሰቃየው ለማን ጥቅም ነው? ለአገርህና ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዳልሆነ አልተረዳህም?ዘረኛው መለስ ዜናዊ አንተን አባሮ የራሱን ጎሳዎች በአንተ ስፍራ ትክቶ ኩሆምሳ አለቃ እስከ ጀነራል የለውን ሹመት ለነሱ አድሎ አንተ እንደቅኝ አገር ወታደር በማያገባህ ጦርነት ጦር ሜዳ ተልከህ ስትሞት. በአንተ ስም ከአሜእሪካ መንግስት የሚያገኘውን ደሞዝህን ለራስ ዘሮች እያደለ አንተን ሬሳ ጎታች ቤት ጠራጊ አሽከር አድርጎ ሲጭወትብህ አይቆጭህም? ኮንጎና ኮሪያ ዘምተህ እንዳልተሸለምክ እንዳልተመሰገንህ ዛሬ የነፍስ ገዳይ የመለስ ዜናዊ ታማኛ እገልጋይ በመሆን የራስህን ህዝብ ስትገል ነገ መግቢያህ የት ነው? ይህን ሁሉ አሳፋሪ ስራ ስትሰራ ህሊናህ አይወቅስህም? 1981 ክስራህ ከተባረርክ ጀምሮ ብብዙ ሺህ የምትቆጠረው በአዲስ አበባ ስትኖር ጓድኞችህን አሰባስበህ ለምን አንድ ግምባር አትመስርትም? የኢትዮጵያ ህዝብ አሳድጎ አስተምሮ አሁን ላለህበት ደረጃ ሲያደርስህ አንተ በችግሩ ከጎኑ ቆመህ በመርዳትና በማጽናንት ፈንታ የጠላት መሳሪያ ሆነህ የራስህን ህዝብ የምትፈጅ በአለም ብቼኛው አንተ ያኢትዮጵያ ወታደር ብቻ በመሆንህ ፣ሞፈርና ቀምበር ተሸክሞ በከፈለው የግብር ገንዘብ ያስተማረህ አባትህ በጭንቅላቷ ውሃ የተሞላበት እንስራ፣ በጀርባዋ አንተንና እህትህን አዝላ ቆሎና ሽሮ ሸጣ ያስደገችህ እናትህ ሁሉም የኩበት ጭስ ባፈነው ቱካንና ቁንጫ በበዛበት ጉሮኖ ታጉረው ልጆችን ከዛሬ ነገ መጥቶ ይረዳናል አያሉ አንባቸውን ሲያፈሱ አንተ ውለታ ቢስ ሆነህ በመቅረትህ በጣም ታሳዝናለህ ታሳፍራለህ፣ ወላጆችህን
የወላድ መካን አድርገህ ስለአስቀረሀቸው አሁን ጊዘው ሳየጨልም ወጎንችህን እንድትፈልጋቸው በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እንማጸንሀለን.

የመለስ ሶስተኛው ረዳት ትናንትና የሚለውጡት ሽሚዝ ያልነበራቸው ዛሬ በሙስናና በማጭበርበር ሚሊዮነር የሆኑ በጽህይ ብርሃን የድል አጥቢያ አርበኞች በመሆን ተናግረው የሚያናግሩ በጨረሻም ለችግር ለእስር የሚዳርጉ ለገዘብ ማናቸውንም ወንጀል የሚፈጽሙ የአገር ፍቅር ስሜት የሌላቸው የባእድ ቅጥረኞች በብዛት ስለሚገኙ መለስን እንደ አይናቸው ብሌን የሚመለከቱ ህሊና ቢሶች ስልሆኑ መጠንቀቅ የስፈልጋል፣ ስራቸው መስለልና ለወያንዎች መንገር ሰሉሆነ መለስ እነሱን ለማንቀሳቀስ በሚሊዮን የሚቆተር ገንዘብ ያባክናል፥

ይህንን ጽሁፍ ከመደምደማችን በፊት የወደፊት እድላችን እንዴት ነው ብለን እንጠይቅ መለስ ዜናዊ የ 1997 ምርጫ አጭበርብሮ አሸነፍኩ በማለት አሁን ደግሞ የወረዳና የቀበሌ ምርጫ አደርጋለሁ ብሎ ህዝቡን ያተራምሳል፣ በአገር ቤትና በውጭ አገር ያሉ ተቃዋሚዎች ምን የላሉ. ተባብረው በህብረት ይታገላሉ ውይስ ዋናውን ጠላታችውን መለስን ትተው እርስ በርሳቸው ይሻኮታሉ? ባለፈው አምስት ወራት የነበረው አልመግባባት አጅግ ይሚያሳዝን የሚያሳፍርም ነበር መለስ ያገኘውን የጦር መሳሪየ ገዝቶ ከኛ እልፎ አሬትሪያን ስለአስደነገጠ በባድሜ ላይ ያላትን የአልኝታ ጥያቄ በችካሉ ፈንታ በወረቀት ተስሎ ይሰጠኝ ብላለች፣ መለስ ያለውን የጦር ሀይል በሙሉ የአየር ሀየሉን ሳይቀር ወደ ትግራይ ልኮ የኛን እንቅስቃሴ የዳምጣል፣ እኛ እንደሱ ነፍስ ገዳይ ስለአልሆንን አዳፍኄና መትረየስ አያስፈልገንም. የእኛ ችግር በህብረት ለመታገል አብረን መቆም ነው፣ አሁን ወደድንም ጠላንም አጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ መስለፍ ተገደናል. ትልቁ ችግራችን አንድ መሪ ማጣት ነው.

ታግሎ የሚያታግለን ደፋር ቆራጥ የበላይ ዘለቀን ሱሪ የታጠቀ የአበበ አረጋይ የገረሱ ዱኪ መንፈስ ያለው ያስፈልገናል፣ ጎበዝና ጀግናን የሚፈጥረው ጊዜና ችግር ስለሆነ ይህ መሪያችን በግድ ወንድ ብቻ መሆን የለበትም፣ የጣይቱን ቀሚስ የለበሸ ብልህ እመቤት ካለሽ ጥሪን እንከተላለን፣ መለስ ዜናዊ በአንድ ክብ ጠረጴ ተቀምጠን በመካከላችን ያለውን ልዩነት አስውግደን አገራችንን በሰላም በጋራ እንምራ በለን ደጋግመን ብንጠየቅ አሽፈረኝ ብሏል፣ የሱ ፍላጎት በመሳሪያ እያስፈራራ እየገደለም ስልጣኑን ሊቀጥልበት ስልሚፈልግ፣ እኛ ደም ሳናፈስ ህይወት ሳናጠፋ በሰላማዊ ሰልፍ ብቻ መለስ ዜናዊን ከምንሊክ ቤተ መንግስት ልናባርረው ተዘጋጅተናል፣ በአንድ በተወሰን ቀንና ሰአት በመላ ኢትዮጵያ ሴት ወንድ ትንሽ ትልቅ ሳንል መሰለፍ ይገባናል፣ ሰልፉ ለሶስት ቀናት ያለማቋረጥ ሲደረግ ለሶስት ቀናት የሚሆን ምግብና ውሀ ይዘን መምጣት የስፈልገናል፣ መልስ ዜናዊን ይዘን እስክናስረው ውይም ከአገር እስኪኮበልል ድረስ መግቢያና መውጫውን መዝጋት ይገባል፣ ጎረበታችን ኬንያ ተመሣየይ ችግር ሲደርስባቸው ባንድ ወር ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች ሞተዋል.፣ ኬንያ አስራ ስድስት ሚሊዮን ህዝብ ሲኖራት አንድ ሺህ ህዝብ መስዋእት ስታደርግ እኛ ከሰባ ስመንት ሚሊዮን ህዝብ አምስት ሺህ ለመሰዋት ዝግጁ መሆን አሉብን፣ አየፈራን ከመሞት እየታገልን ብንሞት ይሻለናል የህ ሰላማዊ ሰልፍ የሞትና የሽረት ስለሆነ አምስት ሚሊዮን ህዝብ ቢሰለፍ እንደምናሸንፍ ግልጽ ነው. መለስ ፈሪ ስለሆነ እንደልማዱ መተኮሱ አይቀርም. መለስ ሰላማዊ ሰልፍን በጣም ስልሚፈራ ኢምባሲዎችን ልኮ መለማመጡ ስልማይቀር ለሁለተኛ ጊዜ እንዳንታለል መጠንቀቅ አሉብን

ፍራንክፈርት ጥር 30 2000 08፣02 2008

## ለዚህ ጽሁፋችን የሰጠነው አርእስት አንድ ህዝብ ማግኘት የሚገባውን መሪ ያገኛል? የሚል ነው

## ባለፉት ሰባ አመታት ሶስት መሪዎች መርተውናል

## ከሶስቱ ትክክለኛው የቱ ነው?

## ለራሳቸው ጥቅምና ስልጣን ተጠቀሙብን ወይስ ? |

## ለወደፊቱ የምንመርጠው መሪ እንዴት መሆን አለበት?

## ለአራተኛ ጊዜ እንዳይደገም ምን ዋስትና አለን?.

Faxabsender: [redacted] [redacted] [redacted] i

የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡

አልጋ፡ወራሽ፡ተፈሪ፡ጠ፡

የኢትዮጵያ፡ መንግሥት፡ አልጋ፡ ወራሽ፡

ራስ፡ ተፈሪ፡ መኰንን፡

ይድረስ ከክቡር፡ ሙሴ፡ ወርዲንግ፡

የጣሊያን፡ የሮይቴር፡ ኮሶቲት፡ ፕሬዚደንት፡

ሰላም፡ ለርስዎ፡ ይሁን፡

የተወደደ፡ ፕሬዚደንት፡ ሆይ፡ ከኢጣሊያ፡ የሮይቴር፡ ኮሶቲ
ት፡ ጋራ፡ የወዳጅነት፡ መንገድ፡ መዝሙሁን፡ ኅብረትዎ፡ ትዎ፡
ወደድሁ፡ ነገር፡ ግን፡ በየጊዜው፡ የሚደነግጡኝን፡ እንደነ፡ የሙ፡
ግሬዎች፡ የሥጠዩትው፡ የአሜሪካን፡ የመንግሥት፡ ወኪል፡ ወዳጅ፡
ትንቅ፡ ኩምፓኒያ፡ በኢትዮጵያ፡ ገስመናዩ፡ እጅግ፡ አዘንኩ፡
ከዚያ፡ እንደነ፡ በጊዜው፡ ከአገሩ፡ ዝምድ፡ በክውርም፡ የተ
ቀመጠውን፡ ገንዘቡን፡ በአሜሪካን፡ የሮይቴር፡ ኮሶቲት፡ በኩ
ዩ፡ ገንዘብ፡ ወዲያው፡ ዐቅሎት፡ ኩምፓኒያ፡ ፊት፡ ለማስቀመጥ፡
ፃስብ፡ ከዋናው፡ ገንዘብ፡ ወቅሉት፡ ኩምፓኒያ፡ ጋራ፡ እንግኘው፡
የሚጎጋር፡ የአሜሪካን፡ ሰው፡ እንገናኘውም፡ ስለዚህ፡ ይህን፡
በለዚህ፡ ደህና፡ እንደነ፡ ገልጨልዎ፡ ገንዘቡን፡ በሥራ፡
በአሜሪካን፡ ገንዘብ፡ ወዲያው፡ በትንቅ፡ ኩምፓኒያ፡ ለማስቀመጥ፡
የሚያስፈልገውን፡ ነገር፡ እርዳታዎን፡ እንዲያደርጉልኝ፡
በለማወቅ፡ ዐቅዬ፡ ደግ፡ ትርታዎን፡ እለምናለሁ፡

ይኸውም፡ በአሜሪካ፡ የሮይቴር፡ ኮሶቲት፡ ለማስቀመጥ
ያስበኩት፡ ገንዘብ፡ ልክ፡ ከሰ፡ ፻፶፡ ፳፯፡፡ ደርሶ
አዲስ፡ አበባ፡ የካቲት፡ ፳፫ ቀን፡ ፲፱፻፲፬ ዓመተ፡ ምሕረት፡

ራስ፡ ተፈሪ፡ መኰንን።

6